USAID FROM THE AMERICAN PEOPLE

YMCA ETHIOPIA

በትውልዶች መካከል አጋርነትን መፍጠር፤ ለሰላም!

Draft

ሰኔ 2014

ማውጫ

ወወክማ እና ፕሮጀክቱ-----------------------1

ኢትዮጵያ እና ሰላም---------------------------2

የተከናወኑ ተግባራት -------------------------3

በፊት እና አሁን------------------------------4

ድፍረቴን ጨምሮታል-------------------------6

አቅጣጫ ጠቋሚዋ---------------------------7

ሳምንታዊ የቤተሰብ የውይይት ጀምረናል-------8

ሊፈርስ ያለ ትዳር መልሻለሁ-------------------9

የቤት ሥራ ፈጥሮልኛል-----------------------10

ከተወያዮች አንደበት-------------------------10

መልካም ተሞክሮዎች----------------------12

ወወክማ እና ፕሮጀክቱ

የኢትዮጵያ ወጣት ወንዶች ክርስቲያናዊ ማህበር (ወወክማ) በሀገራችን ከተቋቋሙት ወጣት እና ማህበረሰብ ተኮር የበጎ አድራጎት ማህበራት በግንባር ቀደምትነት የሚጠቀስ ሲሆን የዓለምና አህጉር አቀፍ ወወክማ አባል እና መሰረታዊ መርሆዎችን የሚጋራ በቀለም፣ በፆታ፣ በእምነት እና በአመለካከት ልዩነት የማያደርግ የበጎ አድራጎት ማህበር ነው።

የኢወወክማ በአካል የዳበሩ፣ በአዕምሮ የጎለበቱ እና በመንፈስ የጠነከሩ ወጣቶችን ለማፍራት በመስራት ከሰባ (70) ዓመታት በላይ በአዲስ አበባ እና በአምስት (5) ክልሎች በሚገኙ አስር (10) ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶቹ የተለያዩ ፕሮጀክቶችን ቀርጾ እየተገበረ ይገኛል። እነዚህም በአዲስ አበባ (ዑራዔል፣ አራት ኪሎ እና አዲስ ከተማ)፣ በኦሮሚያ (በአዳማ እና ተጂ)፣ በደቡብ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች (በወላይታ ሶዶ)፣ ሲዳማ (ሀዋሳ)፣ በአማራ (ባህርዳርና ደብረማርቆስ) እና በትግራይ (መቀሌና አድዋ) ይገኙበታል።

የኢወወክማ የሚሰራቸውን ስራዎች ውጤታማ ለማድረግ የጉዳዩ ባለቤት ከሆኑት ከወጣቶች እና ሴቶች እንዲሁም ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ከተለያዩ ቁልፍ የመንግስት እና መንግስታዊ ካልሆኑ ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት በመስራት ላይ ይገኛል። በዚህም ወጣቶችን በሁለንተናዊ መልኩ ለማብቃት የራሱን ሚና በመጫወት ላይ የሚገኝ ተቋም ነው።
የኢወወክማ 4 ቁልፍ የፕሮግራም ፒላርስ አሉት፡-

1.የወጣቶች የሲቪክ እና የአመራር ልማት፤ የወጣቶችን ተሳትፎ ማሳደግ ለሰላምና ለማህበራዊ ፍትህ፣
2. የሥራ ዝግጁነት (ኢኮኖሚያዊ ማጎልበት)፤ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና፣ የኢንተርፕረነርሺፕና የቢዝነስ ክህሎት ድጋፍ
3. የጤና እና የአካል ብቃት፤ የስነ ተዋልዶ ጤና ፣ ኤችአይቪ መከላከል ተግባራት እና የአካል ብቃት እንቅስቃሴዎች
4. የማህበረሰብ መቋቋም እና ምላሽ፤ የህጻናት እንክብካቤ እና ትምህርት፣ ደህንነቱ የተጠበቀ እና አካታች ከተማዎች እና ማህበረሰብ መፍጠር ናቸው።

በዚሁም መሰረት ድርጅታችን ከUSAID በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ ከ Dexis Consulting Group ጋር በመተባበር **“Dialogue for Supporting Inter-generational Partnerships for Peace”** የተሰኘ ፕሮጀክት እየተገበረ ይገኛል። በዚህ ፕሮጀክት አማካይነትም ከወጣቶችና ከአዋቂዎች የተወጣጡ በባህር ዳር 75 እንዲሁም በአዳማ 75 በድምሩ 150 የሰላም አምባሳደሮችን **“በሰላም፣ በሰላም ግንባታ እና ትብብርን በማጠናከር”** ዙሪያ ሰልጥነው ተመርቀዋል።

በነዚህ በሰለጠኑ የሰላም አምባሳደሮች አማካይነት 1500 በአዳማ እና 1500 በባህርዳር በድምሩ 3000 የተለያዩ የማህበረሰብ ክፍሎችን ተደርሷል። ውይይቱ በዋናነት ወጣቶችን፣ አዋቂዎችን፣ የሀገር ሽማግሌዎችን፣ የሀይማኖት አባቶችን፣ ከሰላም እና ጸጥታ ጋር የሚሰሩ ባለሙያዎችን አሳትፏል። ተሳታፊዎችም **“በሰላምና ሰላም ግንባታ፣ ሀገር በቀል የሰላም ግንባታ እሴቶችን እንዲሁም ትብብርና ውይይትን በማጠናከር ዙርያ”** ስልጠና እንዲያገኙ ተደርጓል። በተጨማሪም 1500 በአማርኛ እና አፋን ኦሮሞ ቋንቋዎች የተዘጋጁ **ሰላምንና መተባበርን** የሚያጠናክሩ ብሮሸሮች/በራሪ ወረቀቶችን በማዘጋጀት ለማህበረሰቡ ግንዛቤ እንዲፈጥሩ ተሰራጭተዋል።

በተጨማሪ **“በወጣቶችና በአዋቂዎች መከካል ትብብርን ማጠናከር-ለሰላም”** በሚል መሪ ቃል በአዳማ እና በባህርዳር ከተሞች ሁለት ክልል አቀፍ ወርክሾፖች ተዘጋጅተዋል። እንዲሁም በአዳማ እና በፌደራል ደረጃ በአዲስ አበባ የሚገኙ ባለድርሻ አካላትና የጉዳዩ ባለቤት የሆኑ ወጣቶችና ሴቶች፣ ጎልማሶች፣ የሀገር ሽማግሌዎች እና የሀይማኖት አባቶች የተሳተፉበት ሀገር አቀፍ የሰላም ግንባታ ወርክሾፕ በአዲስ አበባ በማዘጋጀት **“ሰላምን እንዴት መገንባት ይቻላል እንዲሁም ሰላምን ለመገንባት በትውልዶች መካካል ትብብርን እንዴት መፍጠር ይቻላል”** በሚለው ጉዳይ ምክክር አድርጓል።

ሄለን ተፈራ
የወወክማ ኢትዮጵያ
ፕሮግራምና ም/ዋና ዳይሬክተር

ኢትዮጵያ እና ሰላም

ኢትዮጵያ ለዘመናት አገራዊ ነፃነቷን ጠብቃ የኖረች አፍሪካዊት አገር ናት። ከዚህ እውነታ ጋር የማይነጣጠል የተቃርኖ ታሪክ ባለቤትም ናት - የግጭትና የጦርነት ታሪክ።

የጦርነት ውድመትና የሰላም እጦት ኪሳራ ለኢትዮጵያ አዲስ ሁነት አይደለም። ኢትዮጵያውያን የውስጥና የውጪ ጦርነት ዳፋ ቀማሽ ይሁኑ እንጂ በዚያው መጠን የሰላማዊ አብሮነትና የግጭት አወጋገድ እሴቶች ባለቤት ናቸው።

ሰላም ‘የጦርነት ወይም የግጭት አለመኖር’ ተብሎ የሚወስን ሳይሆን የጦርነት ተቃራኒ ከመሆን የሚልቅና ከዚህ በእጅጉ የሚሰፋ እውነታ ነው።

የሰላም እጦት ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያንን ብዙ አስከፍሏል- ማህበራዊ አብሮነት ሻክሯል፤ የዜጎች ሕይወትና ንብረት ጠፍቷል፤ የአገሪቱ መልካም ገፅታ ጎድፏል … ብሎም አገራዊ እድገቱ አዝጋሚ ሆኗል። በጦርነት ወጪ አሊያም የጦርነትን ውድመት መልሶ በመገንባት አዙሪት ውስጥ ለዘመናት የዘለቀችው ኢትዮጵያ ለሰላም ባህል ግንባታ የሚሆኑ አስፈላጊ እሴቶች እንዳሏት እሙን ነው። ታዲያ ለኢትዮጵያ ዘላቂ ሰላም ግንባታ አስፈላጊ የሆኑ እሴቶችንና አገር በቀል ብልሃቶችን ከትውልድ ወደ ትውልድ ማሸጋገር የግድ ይላል። በአዋቂዎችና ተተኪ ወጣቶች መካከል የትብብር ድልድይ በማነፅ አገራዊ የግጭት አፈታት ባህልንና የሰላም መስተጋብር እሴቶችን ማሳደግ የሁሉም ኢትዮጵያውያን ዜጎች፣ ተቋማትና አደረጃጀቶች ኃላፊነት ነው።

ለበርካታ አስርት ዓመታት በወጣቶች ማኅበራዊ ተሳትፎ፤ የክህሎት እድገትና የተለያየ እድል ፈጠራ ላይ በመሥራት የዘለቀው ወወክማ የዓመታት ልምድና ተቋማዊ አቅሙን በመጠቀም ለኢትዮጵያ ዘላቂ ሰላም ግንባታ በUSAID የገንዘብ ድጋፍ በመሥራት ላይ ይገኛል።

ፕሮጀክቱ በተለይ በኦሮሚያ (አዳማ) እና በአማራ (ባህርዳር) ክልሎች ላይ መተግበሩ ለአገራዊ ሰላም ግንባታው ልዩ ሚና ይኖረዋል። ሁለቱ ክልሎች በሕዝብ ብዛት እና በቆዳ ስፋት አንደኛ እና ሁለተኛ ናቸው። በዚሁ የተነሳም ከአብዛኛው የአገሪቱ ክፍሎች ጋር ይጎራበታሉ። ኦሮሚያ ለምሳሌ- ከትግራይ ክልል በቀር ከሁሉም ክልሎች ጋር ውስጣዊ ድንበርን ይጋራል።

በዚህ ምክንያት ሁለቱ ክልሎች ለሰላም ግንባታ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ቢኖራቸውም አልፎ አልፎ የሰላም መደፍረሶች ይስተዋልባቸዋል። ፕሮጀክቱ በሁለቱ ክልሎች የሰላም ግንባታ ጥረት ውስጥ ጉልህ ሚና መጫወት የሚችሉ ወጣቶችን፣ አዋቂዎችን፣ ሴቶችን፣ የሃይማኖትና የማኅበረሰብ መሪዎችን በማሰልጠን በርካታ የሰላም አምባሳደሮችን ፈጥሯል።

ከሁለቱ ክልሎች የተመለመሉ በጎ ፈቃደኞች በሰላም ግንባታ ላይ ያተኮረ ስልጠና ወስደዋል። እነዚህ የሰላም አምባሳደሮች በወጣቶችና ጎልማሶች መካከል የሚደረገውን የትውልድ ትስስር በማጠናከር ጉልህ ሚና እየተጫወቱ ይገኛሉ።

ላለፉት ስምንት ወራት የሙከራ (pilot) ትግበራ ላይ የዘለቀው ይህ ፕሮጀክት በትውልዶች መካከል ውይይትን የማጠናከርና የሰላማዊ አብሮነት ግንዛቤ የማስጨበጥ ተግባራትን አከናውኗል።

የተከናወኑ ተግባራት

ፕሮጀክቱ በዋነኝነት ስልጠናዎችን በመስጠትና ኮንፈረንሶችን በማከናወን ሲተገበር ቆይቷል፡፡ ስልጠናው የተጀመረው 12 (6 ከአዳማ 6 ከባህር ዳር) ማስተር አሰልጣኞችን በማሰልጠን ነበር፡፡ ከ12ቱ (6 ሴት) ሰልጣኞች ውስጥ ስምንቱ ወጣቶች ሲሆኑ አራቱ ደግሞ አዋቂዎች ነበሩ፡፡ በመቀጠል 12ቱ ማስተር አሰልጣኞች በየክልላቸው 75 የሰላም አምባሳደሮችን አዘጋጅተዋል፡፡ ይህም በሁለቱም ክልሎች በአጠቃላይ 150 የሰላም አምባሳደሮች ሊሰለጥኑ ከአጠቃላይ ሰልጣኞች ግማሽ ያህሉ (50%) ሴቶች ናቸው፡፡ በእድሜያቸውም 50 ያህሉ አዋቂዎች ሲሆኑ 100 ደግሞ ወጣቶች ናቸው፡፡ በመጨረሻም 75ቱ የሰላም አምባሳደሮች ወደ ማኅበረሰቡ በመውረድ (Grass root dialogue)፤ በአዳማ ለ1500 ሰዎች (479ሴ) ፣ በባህርዳርም ለ1500 ሰዎች (560 ሴ) ግንዛቤ ፈጥረዋል፡፡

ስልጠናዎቹ ከላይ በተጠቀሰው መልኩ ከተጠናቀቁ በኋላ በአዳማና በባህርዳር ክልላዊ ኮንፈረንሶች ሲካሄዱ በአዲስ አበባ ደግሞ ሀገር አቀፍ ኮንፈረንስ ተካሂዷል፡፡

ኮንፈረንሱ "በወጣቶችና በአዋቂዎች መካከል ትብብርን ማጠናከር፤ ለሰላም" በሚል መሪ ቃል በወጣቶች፣ በአዋቂዎች፣ በማህበረሰቡ ተወካዮችና በቁልፍ ባለድርሻ አካላት ንቁ ተሳትፎ ተከናውኗል፡፡ በባህርዳር ከተሳተፉት 43 (15ሴ) ሰዎች 24ቱ አዋቂዎች ሲሆኑ የተቀሩት 19 ደግሞ ወጣቶች ናቸው፡፡ በአዳማም 43 (18ሴ) ሰዎች ሲሳተፉ 24ቱ አዋቂዎች የተቀሩት 19 ደግሞ ወጣቶች ነበሩ፡፡ በአዲስ አበባ 40 (25ሴ) በኮንፈረንሱ ሲሳተፉ 11 አዋቂዎች 29 ደግሞ ወጣቶች ነበሩ፡፡

በስልጠናውም ሆነ በኮንፈረንሱ ከእድሜና ከፆታው መሰባጠር ውጪ የተለያዩ የማኅበረሰብ ክፍሎችን የሚወክሉ ተሳታፊዎች እንዲገኙ ተደርጓል፡፡ ይህም

- የሃይማኖት አባቶች፣
- አባ ገዳዎችና ሽማግሌዎች፣
- የእድር አመራሮችና አባላት፤
- እንደ ቤተሰብ መምሪያና ወወክማ ያሉ ድርጅቶች ውስጥ በበጎ ፈቃደኝነት የሚያገለግሉ ወጣቶች፣
- በተለያዩ የትምህርት ቤት ክበቦች ውስጥና በሚኒ ፣ ሚዲያ ላይ የሚሳተፉ ተማሪዎች
- የመንግሥት ሠራተኞች (ከሰላምና ፀጥታ ቢሮ፣ ከሴቶችና ህፃናት፣ ከሰላም ሚኒስቴር...)፣
- ከህግ አካላት (ፖሊሶች፣ ጠበቆች ...)፣ የዩኒቨርሲቲ መምህራን፣
- የቤት እመቤቶች፣ አባወራዎች፣ ጡረተኞች...

ይገኙበታል፡፡

- “ለልጁ ሰላም ብሎ ስም የሚያወጣ ሰው አለ...”
- “በሽታውን ያላወቀ መድሃኒት አይገኝለትም ...”
- “ለመሮጥ ፣ መራመድ መጀመር ይገባል... ”

በፊት እና አሁን

ከስልጠናውና ከውይይቱ ብኋላ ከተወያዮች ጋር በነበረ ቆይታ፤ ከመሳተፋቸው በፊትና ብህዋላ ስላለው ጉዳይ እንዲህ በማለት ገልጠዋል::

- ‘ሰላም ካለ ጦርነት የለም።’ የሚለውን ብቻ ነበር የማውቀው። ሰላምን ለማስከበር ዋነኛው ተጠያቂም መንግሥት ነው ብዬ ነበር የማምነው።

አሁን ግን ጦርነት ሳይኖርም ሰላም ላይኖር እንደሚችል አውቄያለሁ። ሰላም ምንም ችግር ሳያጋጥም ወጥቶ መግባት ብቻ አይደለም። ረሀብ፣ ድህነት ችግር፣ ጤነኛ ያልሆነ የሰዎች መስተጋብር የመሳሰሉትም ከሰላም ጋር መገናኘታቸውን አውቄያለሁ።

- የትኛውም ማህበረሰብ ጠዋት “ሰላም አደራችሁ” ከሚለው ጀምሮ ቀኑን ሙሉ ስለ ሰላም በተለያየ መልኩ ሳይነሳ አይውልም። ስለዚህ ሰላም የለንም እንጂ ስለ ሰላምማ እናውቃለን። ስለ ሰላም ስልጠና ምን ያስፈልጋል?› ብዬ ነበር።

በስልጠናው ግን ሰላምን በዝርዝር ስለ ትርጉሙ፣ ሰላምን ስለሚያደፈርሱ ጉዳዮች፣ ስለ ኃላፊነታችን፣ ስለ ሀገራዊ ችግር መፍቻ ዘዴዎች በማወቄ ደስተኛ ነኝ። እንደውም እንዲህ የጠለቀ እውቀት ኖሮን ቢሆን ኖሮ እስከዛሬም ብዙ ውጤቶችን እናይ ነበር። ለምሳሌ እዚህ ስልጠና ላይ የተሳተፍን ሰዎች ከሌላው ማህበረሰብ የተለየ ግንዛቤውን ስላገኘን የተሻለ ሥራ እንሠራለን ብዬ አምናለሁ። የሰላም አምባሳደርም ሆነን ብዙ ነገሮችን እንቀይራለን።

- ድሮ አንድን ጥቃት አድራሽ በሕግ አምላክ ካልከው ዞሮ ይመለሳል። የአሁን ወጣት እንደዚህ አይደለም። ስለዚህ ለሰላም መደፍረስ ተጠያቂው ወጣቱ እንደሆነ ነበር ያለኝ ግንዛቤ። ‹የኔ ድርሻ ምንድን ነው?› ብዬ ጠይቄ አላውቅም።

“አሁን ግን እኛ ለወጣቱ ምን አስተማርነው?” የሚለውን እንድንጠይቅ አድርጎናል። ሰላም ከራስ እንደሚጀምር አውቄያለሁ። ስልጠናው ላይም ከወጣቶች ጋር እንዲህ እንድንወያይ መደረጉ ራሳችን እንድንጠይቅ አድርጎናል።

በፊት እና...

- ችግርን ለመፍታትና ሰላምን ለማረጋገጥ ኢትዮጵያኖች አንችልም የሚል ድምዳሜ ላይ በመድረሴ ተስፋ ቆርጬ ነበር፡፡

  አሁን ግን ሀገራዊ እውቀቶችን ተጠቅመን፣ በየአካባቢው ያሉ የችግር አፈታቶችን አጥንተንና ተጠቅመንባቸው ሰላማችንን ኢትዮጵያዊ በሆነ ሥነ-ሥርዓት ማምጣት እንደምንችል አውቄያለሁ፡፡

- ሰላም ለብዙዎቻችን አስፈላጊ እንደሆነና እንደምንፈልገው ሁሉ ሰላም በማጣታችን የሚጠቀሙ አካላት እንዳሉ በነበረን ውይይት አውቄያለሁ፡፡ ለነሱ መንገድ ባለመክፈት ሰላምን ማምጣት እንደሚገባን ተረድቻለሁ፡፡

- ለልጁ “ሰላም” እያለ ስም በሚያወጣበት ማህበረሰብ ውስጥ ሰላም ማጣታችን ይገርመኝ ነበር፡፡

  ለካስ እንዲህ በጥልቀት ስለማንወያይበትና ስለሰላም ያለን እውቀት አነስተኛ በመሆኑ ነበር የተቸገርነው የሚል ግንዛቤ አግኝቻለሁ፡፡

- በሽታውን ያላወቀ መድኃኒት እንደማይገኝለት እንዲህ ስለ ሰላም ቁጭ ብለን ካልተወያየንና ግንዛቤያችንን ካላሰፋን ሰላምን ማምጣት አስቸጋሪ እንደሆነ ግልፅ ሆኖልኛል፡፡

- በአሁኑ ወቅት በተለያዩ የሀገራችን ክፍል ከምናየው አንስቶ በቅርባችን በአካባቢያችን በጎረቤታችን ሰላም በማጣታችን በሰላም ዙሪያ ተስፋ ቆርጬ ነበር፡፡

  አሁን ግን የተፈጠረው ተፈጥሯል፡፡ ወደፊት ይህ እንዳይደገም ያደረግነው ውይይት መነቃቃትን ፈጥሮልኛል፡፡ ለመሮጥ መራመድ መጀመር እንደሚገባን እኔ ዛሬ የሰላም አምባሳደር ሆኜ ስለ ሰላም በአካባቢዬ መስበክ ብጀምር ቀስ በቀስ ሀገር ሁሉ ሰላም እንደሚሆን ተረድቻለሁ፡፡

ድፍረቴን ጨምሮታል

ከስልጠናው በኋላ በቤተሰባችን ውስጥ የሚፈጠሩ አለመግባባቶችንና በትምህርት ቤት ውስጥ በጓደኞቼ መካከል የሚከሰቱ ግጭቶችን በቀላሉ እንዲፈቱ የማድረጌ አቅም ጨምሯል። በፊትም እንዲህ ዓይነት ተግባር የማከናውን ቢሆንም ከስልጠናው በኋላ ያገኘሁት እውቀት ድፍረቴን ጨምሮታል። ከዚህ በተረፈ ከስልጠናው ያገኘሁትን እውቀት በሙሉ ላገኘኋቸው ጓደኞቼ አጋርቼያለሁ። በእርግጥ ይህንን ሳደርግ "አንቺ ልጅ አይደለሽ እንዴ? ምነው አሽማጋይ ነኝ አልሽ!" በማለት ሊፈታተኑኝ የሚሞክሩ ሰዎች አልጠፉም።

ስንዱ ምትኩ

ከፊት አውራሪ ሁለተኛ ደረጃ መሰናዶ ትምህርት ቤት 12ኛ ክፍል፤ ከ75ቱ ሰልጣኞች

ከስልጠናው በኋላ መጀመሪያ ያደረግኩት ስለ ሰላም ለራሴ ደጋግሜ ነግሬዋለሁ። ብዙ ጊዜ አንድ ችግር (ፀብ) ሲፈጠር “የራሳቸው ጉዳይ ነው” ነበር የምንለው። አሁን ግን እንዲህ ዓይነት ነገር ሲገጥመኝ “የኔ ድርሻ ምንድን ነው?” ብዬ እንድጠይቅ ሆኛለሁ፡ ሌላው ባህላችን በቤተሰብ መካከል (በእናትና በአባት) ችግሮች ሲከሰቱ እራሳቸው ይፍቱት ነው እንጂ የሚባለው ልጅ አይገባም። ስልጠናውን ከወሰድኩ በኋላ “ሰላም ከራስ ብሎም ከቤተሰብ ይጀምራል። ስለዚህ በእናንተ መካከል በሚኖሩ ጉዳዮች ሁሉ እኔን ስለሚመለከተኝ የራሴ ድርሻ እንዲኖረኝ እፈልጋለሁ” የሚል ውይይት አንስቼ ተስማምተውበታል። በዚህም መሰረት በቤት ውስጥ በሚከሰቱ ጉዳዮች ላይ ንቁ ተሳታፊ አድርገውኛል። ግጭቶች ሲነሱ እኔ ዳኛ ሆኜ እወስናለሁ ማለት ግን አይደለም። በጉዳዩ ላይ አቅጣጫ እየጠቆምኩ ራሳቸው በቀላሉ እንደፈቱ እያደረኩኝ ነው።

ትእግስት ደጀኔ፡-
ከፊት አውራሪ ሁለተኛ ደረጃ መሰናዶ ትምህርት ቤት 11ኛ ክፍል፤ ከ75ቱ ሰልጣኞች

ሳምንታዊ የቤተሰብ የውይይት ጀምረናል



ከሥራዬ አንፃር ስለ ሰላም የተለያዩ ግንዛቤዎች ቢኖረኝም ስልጠናው ሰላምን ፍፁም በተለየ መልኩና በስፋት እንድረዳ አድርጎኛል። ይህ እውቀት ደግሞ ከሥራዬ አንፃር አስፈላጊና ጠቃሚ ሆኖ አግኝቼዋለሁ። ሥራዬ የተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎችን ማለትም ወጣት፣ አዋቂዎች፣ አባ ገዳዎች፣ የሀገር ሽማግሌዎች፣ የሃይማኖት አባቶች ጋር የሚያገናኝ ነው። ይህ ስልጠና ሰላም ከብዝሀነት ጋር፣ ከህግ፣ ከሀገር በቀል እውቀቶች ጋር ያለውን ትስስር በግልፅ ስላሳወቀኝ ሥራዬን በቀላሉ እንድሠራ ረድቶኛል።

ከዚህ ባለፈ ከስልጠናው በኋላ በቤተሰቤ ላይ ከፍተኛ ለውጥ መጥቷል። በመጀመሪያ አስቸጋሪ ባህሪ ያላትን የቤተሰቤን አባል ወደ ስልጠናው ሄዳ በሚቀጥለው ዙር እንድትሰለጥን አደረኳት። በመቀጠል በቤት ውስጥ ከቤት-ሰራተኛዬ ጀምሮ ሁሉንም አባል ሰብስቤ ሳምንታዊ የቤተሰብ የውይይት ጊዜ እንዲኖረን አድርጌያለሁ፡ ሳምንታዊ የውይይት ጊዜ ተጠቅመን የተለያዩ ጉዳዮችን በመቻቻል፣ በመነጋገር፣ በመወያየት፣ በመረዳዳትና ሌሎች ሰላማዊ መንገዶችን በመጠቀም በርካታ ጉዳዮችን ፈተናል። ይህ ትልቅ እርምጃ በቤተሰቤ መካከል ያለውን ፍቅር በመጨመር እንድንነፋፈቅ አድርጎናል።

ሰላማዊት ደበሌ
አዳማ ከተማ አስተዳደር ፅጥታ ቢሮ
ሁለተኛ ዙር ሰልጣኝ

የምሠራው የራሴ ፀጉር ቤት ውስጥ ነው።
እንደ አጋጣሚ ሆኖ ከደንበኞቼ ጋር በማደርገው ውይይት በርካታ ችግሮችን እሠማለሁ። አብዛኛው ችግር የተፈጠረው በአሉባልታ ወሬዎች እንደሆነ ስረዳ አዘንኩ… ለምሳሌ ፀጉሯን ልትሠራ የመጣች ሴት ባሏ እንደሚጠላት ትነግረኛለች። መፍትሄ ብላ የምትወሰደውም ፍቺ እንደሆነ ታምናለች። እንዴት እንደሚጠላት ስጠይቃት የምትነግረኝ አሉባልታ ወሬ ነው። ስለዚህ እርምጃ ከመውሰድሽ በፊት ማወያየት አለብሽ የሚል ምክርን ለግሼያት አሁን ከባለቤቷ ጋር በሰላም መኖር ጀምራለች። ይህ በቤተሰብ ውስጥ አየነው እንጂ ሀገርም እንዲህ ነው ሰላሟ እየደፈረሰ ያለው። ይህ ውጤት የመጣው ስልጠና ከወሰድኩ በኋላ ነው። በአጭሩ የሰላም አምባሳደርነቴን እየተወጣሁ ነው።

እመቤት ጌታቸው
ከማኅበረሰብ
የመጀመሪያ ሰልጣኝ - አዳማ

ስለሰላም ማንኛውም በሥራው ላይ እንደሚንቀሳቀስ ግለሰብ ተመሳሳይ አረዳድ ነበረኝ። በዚህ ኮንፈረንስ ላይ በነበረው ውይይት ሰላምን እንዲህ በተለየ አቅጣጫ አሰላስየው እንደማላውቅ ተረዳሁ። ለሰላም ምን ማድረግ እንዳለብኝ ከራሴ ጋር እንድወያይ የቤት ሥራ ፈጥሮብኛል።

አጥላው ተ/ጻዲቅ

ከአዲስ አበባ ሴቶች ህፃናትና ማኅበራዊ ጉዳይ ቢሮ

ከተወያዮች አንደበት

በክልላችን ምን ያህል ውድመት እንደደረሰብን እናውቃለን። የንብረት፣ የሰው፣ እንደ አጠቃላይ የሀገር ውድመት ደርሶብናል። ይህ ሁሉ የመጣው ከሽኩቻና እንደዚህ ቁጭ ብለን ስለሰላም ስላልተነጋገርን ነው።

ከዚህ በኋላ ጥሩ ጀምራችኋል፣ ቀጥሉበት እኛም ቀበሌ ድረስ ወርደን ስለሰላም እንሰራለን።

ይገረም-ባህር ዳር

በአንፃሩ ድሮ ሰላም ነበርን። አሁን ሰላም ያጣነው ፈረሀ እግዚአብሔር ስለሌ ነው። ድሮ ሰው ሊያጠቃ የመጣን "በህግ አምላክ" ከተባለ ምልስ ይላል፣ ሽምግልና ይከበራል፣ ባልና ሚስት እንኳን ከባድ ችግር ገጥሟቸው ከሽምግልና አያልፍም ነበር። አሁን ያ ነገር የለም። ትግራይ ውስጥ በነበረው ከመንግሥት ጋር ያለመግባባት ችግር ሴት ሽማግሌዎች ተልከው ነበር፤ የሚሰማቸው አልነበረም። ይህ ከማሳዘኑም በላይ ለወጣቱም ያስተላለፈው መልእክት አደገኛ ነበር። ይሄው ችግራችንም እየተፈታ አይደለም።

ስልጠና ላይ ከወጣቶች ጋር በነበረን ውይይት ስለዚሁ ጉዳይ ረጅም ሰዓት ወስደን አውግተናል። ወጣቱ አሁን ችግር ሊፈጥር የመጣን ሰው በሕግ አምላክ ቢሉት ስለማይመለስ ምርጫቸው ቀድሞ ማጥቃት፣ መከላከል ወይ ማምለጥ ነው እንጂ በፍፁም በሕግ አምላክ ቢሉ የሚሰማቸው የለም። አሁን የገባንበትን የሰላም ችግር ለመፍታት እንዲህ ዓይነት የልምድ ልውውጥ መልካም ነው፡

ደመወዝ - ባህር ዳር

ዘንድሮ በነበረው ግጭት ሀገርን ሰላም ለማድረግ በሚል አፋር ክልል ላይ ዘምቼ ነበር። ብዙ ስቃዮችንና ግፎችን አይቻለሁ።
ከጦርነቱ ከተመለስኩ በኋላ የሀገር ሽማግሌ ሆኛለሁ። ስለሰላም ስልጠና አለ ተብዬ ስመረጥ እጅግ ደስ ብሎኝ ነው የመጣሁት። ችግሩን ቀምሼዋለሁ።

ሁላችንም ሰላምን ማዳረስ ይኖርብናል።

ወታደር ከፍያለው በለጠ- ባህር ዳር

በክልላችን እንደምናየው የሰላም ሁኔታው ከጊዜ ወደ ጊዜ ቀስ እያለ እየተባባሰና አሳሳቢ እየሆነ ነው። ከዚህ ስልጠና በኋላም ቀስ በቀስ እታች ድረስ በመውረድ ሁላችንም ሰላምን ማዳረስ ይኖርብናል።

ፍፁም ካሳሁን
ወወክማ ሰርከስ - ባህር ዳር

መልካም ተሞክሮዎች

- ፕሮጀክቱ በተተገበረባቸው ቦታዎች ከሌላው የሀገሪቱ ክፍል በተለየ ሁኔታ የሰላም እጦት የሚታይበት ነው። በመሆኑም በሁሉም ዙር የነበሩ ሰልጣኞች ጉዳዩ አሳሳቢነት የተረዱ ስለሆነ በስልጠናው ላይ እጅግ የነቃና ጠንካራ ውይይቶች ሲያደርጉ ለመመልከት ተችሏል።

- የሰላም ጉዳይ በቀጥታ የሚመለከታቸው የተለያዩ የመንግስት ሰራተኞች፣ በተለያዩ ድርጅቶች ውስጥ ከህብረተሰቡ ጋር (በተለይ ከወጣቱ ጋር) ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸው በጎፍቃደኞች እንዲሁም የሀይማኖት አባቶች፣ አባገዳዎችና ሽማግሌዎች በስልጠናው መሳተፋቸው ፕሮጀክቱ አላማውን እንዲያሳካ ከመርዳቱም ባለፈ ያገኙትን እውቀት ቶሎ እንዲተገብሩ ረድቷቸዋል።

- የነበሩት አጠቃላይ ስልጠናዎችና ውይይቶች ላይ በወጣትነት፣ ጎልማሳነት እና በአዛውንነት እድሜ ክልሎች ያሉ በመሳተፋቸው ከስልጠናው ባሻገር ሰላምን ለማጣጣምት ታላላቆች ይጠቀሙበት የነበረውን ሰልት በተመለከተ የእውቀት ሽግግር እንዲኖር አድርጓል።

- በነበሩት ውይይቶች አንዱ ትውልድ ሌላኛውን ከመውቀስ (ከመወቃቀስ) አልፎ ባሉት ጉዳዮች ላይ መወያየት እንዲጀምሩ መድረኩ እድል ፈጥሯል።

- አብዛኛዎቹ (ሁሉም በሚባል ደረጃ) ተወያዮች ስለሰላም ለመወያየት አዲስ ነገር ሊያገኙ እንደማይችሉ ግምት ቢኖራቸውም ከስልጠናው በኋላ አጠቃላይ ስለሰላም ያላቸው ግንዛቤ እንደተስተካከለና ተጨማሪ እውቀት ማግኘታቸውን መግለጣቸው

- ተወያዮቹ ለሰላም መደፍረስ ቁልፉ ችግር አለመነጋገር መሆኑን መገንዘብ ውይይት መጀመራቸው፤

- በሁለቱም ክልሎች የነበሩ ተሳታፊዎች ኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ ችግሮችን የመፍቻ ዘዴዎች (በአማራና በሰሜኑ ክፍል - ሽምግልና፣ በኦሮሞ - አባገዳ፣ ሀደ ሲንቄ፣ በጋሞም እንዲሁ) መኖራቸውን መገንዘባቸውና ከነዚህ ትምህርት ወስዶ መፍትሄዎችን ማምጣት እንደሚቻል መገንዘባቸውን መግለጻቸው

- የሰላም ጉዳይ እንደ ሌሎች ማህበራዊ ጉዳዮች የተወሰኑ ሰዎችን የሚመለከት ሳይሆን የሁሉም ጉዳይ መሆኑን በነበሩ አጠቃላይ ውይይቶች ከመገለፁ በተጨማሪ በሁሉም ክልል ላይ የነበሩ ተሳታፊዎች የነበራቸውም ተሳትፎ ይህንኑ የሚያሳይ እኩልና የነቃ መሆኑ

- ተሳታፊ የነበሩ የተለያዩ ተቋማት ለአብነት፡ ከሰላምና ፀጥታ ቢሮ፣ ከሴቶችና ህፃናት፣ ከሰላም ሚኒስቴር፣ ከህግ አካላት፣ ከሃይማኖት አባቶች፣ ከአባ ገዳዎችና ሽማግሌዎች፣ ከእድር አመራሮች፤ ከበጎ ፈቃደኛ ወጣቶች፣ ከተለያዩ የትምህርት ቤት ክበቦች ውስጥና በሚኒ ሚዲያ ላይ ከሚሳተፉ ተማሪዎች መካከል የእርስ በእርስ ግንኙነት (partnership) እንዲጠናከር መጠየቁና ውይይቱ እንዲቀላጠፍ ፍላጎት መጨመሩ፤

- በህብረተሰቡ መካከል ያለውን የሃይማኖት፣ የዘር፣ የባህል ልዩነት በመረዳት እና በማመን መቻቻል ለሰላም መጎልበት ቁልፍ መሆኑን ግንዛቤ መጨመሩ

- የሰላም አጀንዳ ወቅታዊ ፣ አንገብጋቢ እና ጥንቃቄ የሚያስፈልገው መሆኑን ሁሉም ተወያይ መገንዘብ መቻሉ

- ሰላም የአንድ ወቅት ጉዳይ ሳይሆን ረጅም ሂደትን የሚፈልግ ስለሆነ ፕሮጀክቱ ቀጣይነት እንዲኖረው መጠየቁ፤ ተሳታፊዎችም ባላቸው ግንዛቤ ከራሳቸው ጀምረው ቤተሰብ፣ ጎረቤት .... እያሉ ውይይት እንዲጀመር ለማድረግ መነሳሳት ማሳየታቸው፤ ቃል መግባታቸው እንዲሁም ቃላቸውን መተግበር መጀመራቸው

USAID
YMCA
Supporting Intergenerational Partnerships for Peace
National advocacy workshop and panel discussion with
youths, Adults, Community members and key stakeholders
June 4 th 2022
Addis Ababa, Ethiopia
YMCA

ወወክማ ኢትዮጵያ / YMCA- Ethiopia
ስልክ- + 251 114 701035
ኢሜል- admin@ymcaethiopia.org
ድህረ ገጽ- www.ethioymca.org
ፖ.ሳ.ቁ- 34340